# ሙት አልልህም (ምድሪቱን ሙላት)

ከሕያው ቃል

ድሆ ምን ቤት አለህ፣ የምንስ መኪና፣
ምን 'ሚሉት እልፍኝ፣ ምን ትለው ኩሽና፣
የለህም ፍጽሞ፣ ከሞትክም በኋላ፣
ለዓለም 'ምትተወው፣ ገንዘብ የወርቅ ካዝና፤
ግን ሙት አልልህም፣ ሙት እግርህን ብላ፣
አንተን ባጣች ምድር፣ ኑሮ አይደለምና፣
ይልቁን ንቃበት፣ እንቅልፉን ተውና፣
መቼም ከጉልበትህ፣ "ታከትኩ" ከማያውቀው፣
ከደደረው ጡንቻህ፣ አለት ከሚያደቅቀው፣
ለፍሬ የመረቀው፣ ጭንህ ከብሯልና፣
ገጥግጣት ምድሪቱን፣ ውለድ ውለድና!!
ምናልባት! ምናልባት!
በልጆችህ ትግል፣ በልጆችህ ጥረት፣
ዘመኑ ሲቀየር፣ አዲስ ቀን ሲጠባ፣
ጥቃትህ ሲያበቃ፣
የጎመንህ ምንቸት፣ በገንፎ ሲተካ፣
በተስፋ ተዳፍረህ፣ ከነገው ጎዳና፣
በፌዝ ለመሳለቅ፣ በሞት በእርጅና::